የሰ/መ/ቁ. 32229

ሚያዝያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

አመልካች፡- መሪጌታ ልሣነወርቅ በዛብህ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጠቅላይ ቤ/ክህነት ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ፍቅረማርያም ካሣ ቀረበ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥነ ሥርዓት ሕጉን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በተጠሪ ጽ/ቤት የኦጋዴን ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሆኜ በመስራት ላይ ሣለሁ ከታህሣሥ 1 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ የቁልቢ ነዋየ ቅድሣት ማደራጃ ዋና ፀሐፊ ሆኜ እንድሰራ ተደርጓል፣ ተጠሪው ደረጃዬን ከሥራ አስኪያጅነት ወደ ፀሐፊነት ዝቅ ማድረጉ አግባብ ስላልሆነ ወደ ሥራ አስኪያጅነት ደረጃና ደመወዝ እንድመለስ ይወስንልኝ በማለት ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች የሥራ መሪ ስለሆኑ ቦርዱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም፣ አመልካች ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ በቦታቸው ሌላ ሥራ አስኪያጅ መመደቡን እያወቁ ሣይቃወሙ ቆይተው አሁን ያቀረቡት ክስና የክፍያ ጥያቄ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ቦርዱም አመልካች የሥራ መሪ ስለሆኑ ቦርዱ ክሱን ተቀብሎ የማየት ሥልጣን የለውም፣ ክሱ ግን በይርጋ የታገደ ነው በማለት ክሱን በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡

በመቀጠልም አመልካች ይህንኑ ክስ ለፌዴ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት አቅርበው ተጠሪ በሰጠው መልስ ክሱ ቀደም ሲል ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ቀርቦ ቦርዱ ውሣኔ የሰጠበት ስለሆነና ፍ/ቤቱ ደግሞ ይግባኝ ሰሚ ስላልሆነ



ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚለውንና ሌሎች መከራከሪያዎችን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ቦርዱ በዚህ ዓይነቱ ክርክር ላይ የዳኝነት ሥልጣን ሣይኖረው በክርክሩ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ ስለማይኖር ፍ/ቤቱ የቦርዱን ብይን የሚረዳው ክሱ በይርጋ ቀሪ ቢሆንም ቦርዱ ጉዳይን የማየት ሥልጣን የለውም የሚል መሆኑን ነው፣ ስለዚህ አመልካች አሁን ክሱን ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ያቀረቡ ስለሆነ በዚህ ረገድ ተጠሪ የፍ/ብሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5ን በመጥቀስ ያነሣው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም በማለት ብይን ከሰጠ በኋላ ተጠሪ አመልካችን ከሥራ አስኪያጅነት ወደ ሌላ የሥራ መደብ የለወጣቸው ያለአግባብ በመሆኑ ተጠሪ አመልካችን ቀድሞ ወደነበሩበት የሥራ መደብ /ወደ ሥራ አስኪያጅነት/ በመመለስ በመደቡ የሚከፈለውን ደመወዝና አበል ሊከፍላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ቀደም ሲል ክሱ ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ቀርቦ ቦርዱ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ሲል ብይን ሰጥቶበታል፣ ብይኑ ይግባኝ ተብሎበት በፍርድ ውሣኔ አልተሻረም፣ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የቀረበለትን ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ውድቅ ማድረግ ሲገባው ይህ ያልተሻረ ብይን እያለ ጉዳዩን መርምሮ ውሣኔ መስጠቱ አግባብ ስላልሆነ የፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል በማለት ወሰነ፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘትም ባጭሩ የሥር ፍ/ቤት ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት መወሰኑ የሕግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን ይህ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ሥልጣን የለኝም ሲል ከወሰነ በኋላ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት በብይኑ ላይ ማስፈሩ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት

ያቀረቡት ክስ ቀደም ሲል ውሣኔ አግኝቶ የበቃ ነው ለማለት የሚያስችል መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች በመጀመሪያ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ክስ አቅርበው ቦርዱ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የለኝም እንጂ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ሲል መበየኑን፣ በመቀጠልም አመልካች ክሱን ለፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት አቅርበው ተጠሪ ጉዳዩ ቀደም ሲል የቦርዱ ውሣኔ /ብይን/ ያረፈበት ስለሆነ ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ሊታገድ ይገባል የሚል መቃወሚያ ያቀረበ መሆኑን፣ ፍ/ቤቱ ቦርዱ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን ሣይኖረው ይርጋውን አስመልክቶ ብይን መስጠት አይችልም በማለት መቃወሚያውን በብይን ውድቅ አድርጎ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠቱን፣ እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቦርዱ ቀደም ሲል ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ሲል የሰጠው ብይን በይግባኝ ስላልተሻረ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበለትን ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ውድቅ ማድረግ ሲገባው በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠቱ አግባብ አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ የሻረው መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በዚህ መዝገብ የሚያከራክረውን ጉዳይ በየደረጃው ያዩት ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የተለያየ ሲሆን ለዚህ ልዩነት መነሻው ቦርዱ የዳኝነት ሥልጣን የለኝም ነገር ግን ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ሲል የሰጠው ብይን መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ይኸውም የመጀ/ደ/ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለኝም የሚለውን የብይኑን ክፍል ይዞ ውሣኔውን ያሣረፈ ሲሆን ከፍ/ፍ/ቤት ደግሞ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው የሚለውን ክፍል በመያዝ ይርጋውን አስመልክቶ የተሰጠው ብይን ስላልተሻረ ለመ/ደ/ፍ/ቤት ክስ ሊቀርብ አይችልም በማለት ወስኗል፡፡

በመሠረቱ አንድ ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ የመዳኘት ስልጣን ያለው መሆኑን ካላረጋገጠ የግራ ቀኙን ክርክር መመርመር አይጀምርም፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ክሱ ለቦርድ መቅረብ ያልነበረበት መሆኑን ከተገነዘበ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን እንደሌለው በመግለጽ እዚያው ላይ



ማቆም ሲገባው በተጠሪ የቀረበውን የይርጋ ክርክር መርምሮ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል ሀሣብ በብይኑ ላይ አስፍሯል፡፡ ቦርዱ የዳኝነት ሥልጣን ከሌለው ይርጋውንም አስመልክቶ ብይን መስጠት አይገባውም፡፡ ስለሆነም ቦርዱ በአንድ በኩል የዳኝነት ሥልጣን የለኝም እያለ በሌላ በኩል ደግሞ ሥልጣኑ ቢኖረው ኖሮ ሊመረምር ይገባው የነበረውን ጉዳይ በብይኑ ላይ መጥቀሱ ስለይርጋው ብይን ሰጥቷል ለማለት የሚያስችል ስላልሆነ አመልካች ለመ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5 መሠረት ውድቅ የሚያደረግ አይደለም፡፡ በዚህ ምክንያት ቦርዱ ቀደም ሲል ይርጋውን በተመለከተ ብይን የሰጠ ስለሆነ ብይኑ በይግባኝ ሣይሻር ክሱ ለመጀ/ደ/ፍ/ቤት ሊቀርብ አይገባም በማለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 52954 ሰኔ 1 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ብይኑ የተሻረ መሆኑን ተገንዝቦ በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ በመመርመር የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡